www. Ethiopiawinet.net

# ዶ/ር ብርሃኑን ጨምሮ ስምንት ተከሳሾች ንብረታቸው እንዲታገድ ትዕዛዝ ተላለፈ

(በታምሩ ጽጌ)

ራሱን የኢትዮጵያ ነፃነትና ዴሞክራሲ ሃይል ብሎ የሚጠራ ወታደራዊ ቡድን ግንቦት ሰባት ከሚባለው አሸባሪ ቡድን አባላት ጋር ግንኙነት በመፍጠርና በህቡዕ በመሰባሰብ መንግሥትን በሃይልና በአመፅ ለመጣል ተንቀሳቅሰዋል በሚል የፌዴራል ዐቃቤ ሕግ ክስ ከመሠረተባቸው 46 ተከሳሾች መካከል ዶ/ር ብርሃኑ ነጋን ጨምሮ የስምንት ተከሳሾች ንብረት እንዲታገድ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሁለተኛ ወንጀል ችሎት ጥቅምት 26 ቀን 2002 ዓ.ም. ትዕዛዝ አስተላለፈ፡፡ ፍርድ ቤቱ የእግድ ትዕዛዙን ያስተላለፈው የፌዴራል ዐቃቤ ሕግ ጥቅምት 13 ቀን 2002 ዓ.ም. ተከሳሾቹ የሕገ መንግሥታዊ ስርዐቱን በሀይልና በአመፅ ለማፍረስ ሲንቀሳቀሱ የተገኙና በዚሁ ጉዳይ የተከሰሱ በመሆናቸው ንብረታቸው በሙሉ ወይም በከፊል ሊወረስ ስለሚችል ንብረታቸው በሙሉ እንዲታገድለት በጽሕፈት ቤት በኩል ባቀረበው አቤቱታ መሠረት ነው፡፡

ዐቃቤ ሕግ ንብረታቸው በከፊል ወይም በሙሉ ሊወረስ ስለሚችል በሚል እንዲታገድለት አቤቱታውን ያቀረበው፤ የዶ/ር ብርሃኑ ነጋ፣ አንዳርጋቸው ጽጌና ያረጋል ይማም (የሚስጥር ስም ሚኪ) (ሦስቱም በሌሉበት ጉዳያቸው እየታየ ያለና ጥፋተኛ የተባሉ"፣ አቶ ጽጌ ሃብተማርያም፣ ብ/ጄነራል ተፈራ ማሞ፣ አቶ አሳምነው ጽጌ (ብ/ጄነራል የነበሩ"፣ ሌ/ኮሎኔል አለሁበል አማረ እና አቶ ጌቱ ወርቁ ንዳውናቸው፡ ፍርድ ቤቱ መዝገቡን ቀጥሮ የነበረውተ ከሳሾች ያቀረቡትን ሰነድና የተሰየሙትን የመከላከያ ምስክሮች ቃል፤ ዐቃቤ ሕግ ካቀረበባቸው የሰነድና የምስክሮች ቃል ጋር በማገናዘብ ፍርድ ለመስጠት የነበረ ቢሆንም፣ የምስክሮች ቃል ከ800 ገጽ በላይ በመሆኑና የተከሳሽ ጠበቆች ያቀረቡት የመፍረጃ ሀሳብ ሰፊ በመሆኑ እንዳልደረሰለት በመግለፅ ተለዋጭ ቀጠሮ እንደሚያስፈልገው አሳውቋል፡፡

ፍርድ ቤቱ ዐቃቤ ሕግ የጠየቀው አቤቱታ አዲስ ነገር ሆኖ ቢያገኘውም በወንጀለኛ ሕጉ ያለመሆኑንና የሕግ አውጭው መንፈስ ምን እንደሚልካገናዘበ በኋላ አቤቱታው ተቀባይነት ማግኘቱንና ንብረታቸው እንዲታገድ ትዕዛዝ ማስተላለፉን ተናግሯል፡፡

በተከሳሾቹ ስም የተመዘገቡ ንብረቶች ተለዋጭ ትዕዛዝ እስከሚሰጥባቸው ድረስ ባሉበት ሁኔታ ታግደው እንዲቆዩ፣ በማንኛውም መንገድ ለ3ኛ ወገን እንዳይተላለፉ በወ/ሕ/ቁ 98፣ 99 እና 260 መሠረት ትዕዛዝ የተሰጠባቸውን ብረቶች፣ ነጋና ቤተሰቡ ኃ/የተ/የግል/ማ፣ አዲስ መንገድ የቤት ሥራ አ/ማ፣ የኢትዮጵያ የበቆሎ እርሻና ኢንዱስትሪ ማህበር፣ አዲስ ብሮድካስቲንግ ኃ/የተ/የግል/ማ፣ ፈውስ የመድሃኒት ፋብሪካ፣ አርቢት የቤተሰብ አንቶሜቲክ የዓይን ህክምና ክሊኒክና የዓይን መድሃኒቶች አስመጭና ቸርቻሪ የዶ/ር ብርሃኑ ንብረቶች ናቸው፡፡

በካርታ ቁጥር 40345 ተመዝግቦ የሚገኘው 216 ካሬ ሜትር ቦታ ላይ ያረፈ መኖሪያ ቤት ደግሞ የአቶ እንዳርቻው ፅጌ ሲሆን፤ በ500 ካሬ ሜትር ላይ ያረፈ የመኖሪያ ቤትና በአማራ ክልል የሚገኙ አንድ ወፍጮና አንድ መኖሪያ ቤት የብ/ጄኔራል ተፈራ ማሞ ናቸው፡፡

በ200 ካሬ ሜትር ቦታ ላይ ያረፈ የመኖሪያ ቤት፣ በአማራ ክልል የሚገኙ ዝባኖ ኢንተርናሽናል አ/ማ፣ ሆቴል፣ የእርሻ ቦታ ድርሻ፣ የድንጋይ መፍጫ ማሽን ከሌሎች ጋር በጋራ ያላቸው አቶ አሳምነው ጽጌ እና በካርታ ቁጥር 40343 እና 23746 የተመዘገበና 990 ካሬ ሜትር ቦታ ላይ ያረፈ ባለ 4 ፎቅ ሕንፃ የአቶ ጽጌ ኃይለማርያም ንብረት ታግዷል፡፡

አንድነት ኃ/የተ/የግል/ማ፣ ቦሌ ሮክ ጅምናዚየምና ወንድማማቾች መዝናኛ ማዕከል (እምቢልታ ሆቴል) የአቶ ጌቱ ወርቁ ንዳው እና በአንድ ሚሊዮን ብር ካፒታል የተመዘገበ ኢንቨስትመንት ፈቃድ የኮሎኔል አለሁበል አማረ ንብረትና የአቶ ያረጋል ይማም (ሚኪ) ንብረት የሆነው፣ በአራዳ ክፍለ ከተማ የሚገኘው አግሪ የእስንሳት መድሃኒት አስመጪና አከፋፋይ እና የታርጋ ቁጥሩ አ/አ 2-80298 የሆነ ዳማስ ሚኒባስ መኪና እንዲታገድ ትዕዛዝ ተላልፏል፡፡

የተከሳሾች ጠበቆች (የአቶ ጽጌና አቶ ወርቁ) "ይኸ ነገር ለኛ አዲስ ነው" በማለት ዐቃቤ ሕግ ለፍርድ ቤቱ ያቀረበው አቤቱታ በግልባጭ ሊሰጣቸው ይገባ እንደነበር ለፍርድ ቤቱ አመልክተዋል፡፡

የተሰጠው ትዕዛዝ ንብረትን የሚያስከብር በመሆኑ አቤቱታው እንደሚሰጣቸው በመግለፅ በጉዳዩ ላይ ሊከራከሩበት እንደሚችሉ ፍርድ ቤቱ ገል"ል፡፡

ከተከሳሾቹ መካከል አቶ አሳምነው ጽጌ በማረሚያ ቤት እንደ እስረኛ መብታቸው እንዳልተከበረላቸው፣ ቤተሰቦቻቸው እንዳይጠይቋቸው መከልከላቸውን ለፍርድ ቤቱ ሲያመለክቱ፤ ብ/ጄነራል ተፈራ በበኩላቸው የተወሰደው እርምጃ (ንብረት እንዲታገድ) እነሱን ብቻ ሳይሆን ቤተሰቦቻቸውን ጭምር ለመጉዳት የተወሰደ እርምጃ መሆኑን ሲናገሩ፤ ፍርድ ቤቱ፣ ሕጉ ከሚያዘው ስርዓት ውጭ መሆኑን በመግለፅ ንግግራቸውን እንዳልተቀበላቸው ተናግሯል፡፡

ጉዳዩን ፖለቲካዊ ማድረግ እንደሌለባቸው በመግለፅ ፍርድ ቤቱ እየሰራ ያለው የሕግ ጉዳይ ብቻ መሆኑን አስገንዝቧል፡፡ በተከሳሾቹ ላይ ፍርድ ለመስጠትም ለኅዳር 4 ቀን 2002 ዓ.ም. ተለዋጭ ቀጠሮ በመስጠት ችሎቱ ተጠናቋል፡፡